IslamHouse.com

مركز أصول
Osoul Center
www.osoulcenter.com

Amharic
አማርኛ
أمهري

# البرهان
# في وجوب اللجوء إلى الواحد الديان

# ቡርሃን
# አላህን መለመን ግዴታ ስለመሆኑ


አዘጋጅ፡
አብዱላህ ቢን አብዱረሕማን አስ-ሰዕድ

ተርጓሚ፡
ጋሊ አባቦር አባጉማ

እርማት፡
ሼኽ ጀማል ሙሀመድ

# البرهان
# في وجوب اللجوء
# إلى الواحد الديان

تأليف

**عبدالله بن عبدالرحمن السعد**

ترجمة

**الداعية غالي أبا بور**

مراجعة

**الداعية جمال محمد أحمد**

Amharic
አማርኛ
أمهري

**ح المكتب التعاوني للدعوة والإرشاد و توعية الجاليات بالربوة، ١٤٣٩هـ**

**فهرسة مكتبة الملك فهد الوطنية أثناء النشر**

عبدالله عبدالرحمن

البرهان في وجوب اللــجوء إلى الواحد الديان – اللغة الأمهرية. / عبدالله عبدالرحمن السعد.- الرياض، ١٤٤١هـ

٤٨ ص، ١٢ سم x ١٦,٥ سم

ردمك : ٠-٣٣-٨٢٢٩-٦٠٣-٩٧٨

١- الايمان (الاسلام)　　٢- الوعظ والارشاد　　أ. العنوان

**ديوي ٢٤٠　　١٤٣٩/٣٠٩٢**

**رقم الايداع: ١٤٤١/٣٠٩٢**

**ردمك : ٠-٣٣-٨٢٢٩-٦٠٣-٩٧٨**

مركز أصول
Osoul Center
www.osoulcenter.com

This book is the property of the Osoul Center. Permission is granted for it to be stored, transmitted, and published in any print, electronic, or other format - as long as the Osoul Center is clearly mentioned on all editions, no changes are made without the express permission of the Osoul Center, and a high level of quality is maintained.

+966 11 445 4900

+966 11 497 0126

P.O.BOX 29465 Riyadh 11457

osoul@rabwah.sa

www.osoulcenter.com

بسم الله الرحمن الرحيم

በአላህ ስም እጅግ
በጣም ርህሩህ እጅግ
በጣም አዛኝ በሆነው

إن الحمد لله نحمده، ونستعينه، ونعوذ بالله من شرور أنفسنا وسيئات أعمالنا، من يهده الله فلا مضل له، ومن يضلل فلا هادي له، وأشهد أن لا إله إلا الله وحده لا شريك له، وأشهد أن محمدًا عبده ورسوله صلى الله عليه وعلى آله وصحبه وسلم تسليمًا كثيرًا، أما بعد.

ምስጋና ሁሉ ለአላህ ይገባው፡፡ እናመሰግነዋለን፤ እርዳታም ከሱ እንጠይቃለን፡፡ ከነፍሳችን ክፋትና ከስራዎቻችን ጥፋት በአላህ እንጠበቃለን፡፡ አላህ የመራውን ሰው የሚያጠመው ነገር የለም፤ አላህ ያጠመመውን ደግሞ የሚመራው የለም፡፡ ከአላህ ሌላ በሐቅ የሚመለክ አምላክ እንደ ሌለ፤ እሱ ብቸኛ ነው አምሳያ የለውም፡፡ ሙሐመድም (ሰዐወ) የአላህ ባርያና መልእክተኛው መሆናቸውን እመሰክራለሁ፡፡

በመቀጠል፣ በሰዎች ዉስጥ ከተስፋፋና ከተሰራጩ ወንጀሎች መሐከል አንጋፋው፣አላህ ብቻ ማድረግ የሚችለዉን ነገር ሆኖ ሳለ ሌላን አካል መለመን ነዉ፡፡ ለምሳሌ ሀጃዎቻችንን ወይም ጉዳዮቻችንን ማስፈጸም የሚችል፣ ካለንበት ችግር የሚያወጣን፣ የታመመን የሚፈዉስ፣ ልጅ አጥቶ ለተቸገረ ልጅን የሚሰጥ፣ እና የመሳሰሉትን ማድረግ የሚችለዉ አሸናፊዉና ሀያሉ ጌታ አላህ ብቻ ነዉ፡፡ ሆኖም ግን በአሁን ግዜ እነዚህን ከላይ የተጠቀሱትን እና የመሳሰሉትን ጉዳዮች ከአላህ ሌላ ያለን አካል መለመን በሰዎች ዉስጥ እየተስፋፋ እና እየተሰራጨ ያለ ድርጊት ሆኖዋል፡፡ ይህ ድርጊት የጃህሊያ ወይም የአላዋቂዎች

መንገድ ሲሆን በኢስልምና ሀይማኖት ዉስጥ ፍጹም የተከለከለ እና በአላህ ማጋራት እንደሆነም በግልጽ ሊታወቅ ይገባል፡፡

ይህ ስራ ዉድቅ መሆኑን በአስር መንገድ መስረጃ ማቅረብ ይቻላል፡፡

1

# አላህ (ሱወ)

አላህ (ሱወ) መልእክተኛውን ከሱ ሌላን መለመን ከለከለ፡፡ ለተከበረ መልእክተኛው እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَلَا تَدۡعُ مِن دُونِ ٱللَّهِ مَا لَا يَنفَعُكَ وَلَا يَضُرُّكَ فَإِن فَعَلۡتَ فَإِنَّكَ إِذٗا مِّنَ ٱلظَّٰلِمِينَ ﴾

[يونس: ١٠٦]

«ከአላህም በቀር የማይጠቅምንና የማይጎዳን አትገዛ፡፡ ብትሠራም አንተ ያን ጊዜ ከበደለኞቹ ትሆናለህ፡፡››(ዩኑስ፡ 106)

አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَمَنۡ أَضَلُّ مِمَّن يَدۡعُواْ مِن دُونِ ٱللَّهِ مَن لَّا يَسۡتَجِيبُ لَهُۥٓ إِلَىٰ يَوۡمِ ٱلۡقِيَٰمَةِ وَهُمۡ عَن دُعَآئِهِمۡ غَٰفِلُونَ ۝٥ وَإِذَا حُشِرَ ٱلنَّاسُ كَانُواْ لَهُمۡ أَعۡدَآءٗ وَكَانُواْ بِعِبَادَتِهِمۡ كَٰفِرِينَ ﴾ [الأحقاف: ٥-٦]

“እስከ ትንሣኤ ቀን ድረስ ለርሱ የማይመልስለትን አካል ከአላህ ሌላ ከሚጠራ ሰው ይበልጥ የተሳሳተ ማነው? እነርሱም ከጥሪያቸው ዘንጊዎች ናቸው፡፡ ሰዎችም በተሰበሰቡ ጊዜ (ጣዖቶቹ) ለነርሱ ጠላቶች ይኾናሉ፤ (እነሱን) መገዛታቸውንም ከሓዲዎች ይኾናሉ፡፡ (አል-አሕቃፍ፡ 5-6)

አላህ እንዲህ ይላል፡- ‹እነሆ መስጅዶች የአላህ ብቻ ናቸው፤ ከአላህ ጋር አንድንም አትገዙ፡፡› (አልጅን፡ 18). ይህን መሰል መልእክት የያዙ አንቀጾች ብዙ ናቸው፡፡

# 2

# አላህ (ሱወ)

ከሱ ሌላ ያለውን ትተን እሱን ብቻ እንድንለምን አዘዘን አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿وَقَالَ رَبُّكُمُ ٱدۡعُونِيٓ أَسۡتَجِبۡ لَكُمۡۚ إِنَّ ٱلَّذِينَ يَسۡتَكۡبِرُونَ عَنۡ عِبَادَتِي سَيَدۡخُلُونَ جَهَنَّمَ دَاخِرِينَ﴾ [غافر: ٦٠]

“ጌታችሁም አለ፡ ‹ለምኑኝ፤ እቀበላችኋለሁና፤ እነዚያ እኔን ከመግገዛት የሚኮሩት ተዋራጆች ኾነው ገሀነምን በእርግጥ ይገባሉ፡፡› (ጋፊር፡ 60)

አላህ እንዲህ ይላል፡

﴿وَإِذَا سَأَلَكَ عِبَادِي عَنِّي فَإِنِّي قَرِيبٌۖ أُجِيبُ دَعۡوَةَ ٱلدَّاعِ إِذَا دَعَانِۖ فَلۡيَسۡتَجِيبُواْ لِي وَلۡيُؤۡمِنُواْ بِي لَعَلَّهُمۡ يَرۡشُدُونَ﴾ [البقرة: ١٨٦]

“ባሮቼ ከእኔ በጠየቁህ ጊዜ፥ (እንዲህ በላቸው)፡- እኔ ቅርብ ነኝ፤ የለማኝን ጸሎት በለመነኝ ጊዜ እቀበለዋለሁ፤ ስለዚህ ለኔ ይታዘዙ፤ በኔም ይመኑ፤ እነሱ ሊምመሩ ይከጀላልና፡፡› (አልበቀራ፡ 186)

አላህ እንዲህ ይላል፡

﴿أَمَّن يُجِيبُ ٱلۡمُضۡطَرَّ إِذَا دَعَاهُ وَيَكۡشِفُ ٱلسُّوٓءَ وَيَجۡعَلُكُمۡ خُلَفَآءَ ٱلۡأَرۡضِۗ أَءِلَٰهٞ مَّعَ ٱللَّهِۚ قَلِيلٗا مَّا تَذَكَّرُونَ﴾ [النمل:٦٢]

“ያ ችግረኛን በለመነው ጊዜ የሚቀበል፣መከራንም የሚያስወግድ፣

በምድርም ላይ ምትኮች የሚያደርጋችሁ፤ (ይበልጣልን? ወይስ የሚያጋሩት?) ከአላህ ጋር ሌላ አምላክ አለን? ጥቂትንም አትገሠጹም፡፡» ትርጉሙ፡ ከአላህ ሌላ ይህን ማድረግ የሚችል አለን? ማለት ነው፡፡ መልሱም፡ የለም፤ ይህን ማድረግ የሚችለው እሱ ብቻ ነው የሚል ይሆናል፡፡

አላህ እንዲህ ይላል፡

﴿قُلْ أَمَرَ رَبِّي بِالْقِسْطِ ۖ وَأَقِيمُوا وُجُوهَكُمْ عِندَ كُلِّ مَسْجِدٍ وَادْعُوهُ مُخْلِصِينَ لَهُ الدِّينَ ۚ كَمَا بَدَأَكُمْ تَعُودُونَ ﴿٢٩﴾﴾ [الأعراف: ٢٩]

“ጌታዬ በማስተካከል አዘዘ፡፡ በየመስጊድ ዘንድ (እርሱን ለመገዛት) ፊቶቻችሁን አስተካክሉ፡፡ ኀይማኖትን ለርሱ ፍጹም አድርጋችሁ ተገዙት፡፡ እንደ ጀመረያችሁ ትመለሳላችሁ› በላቸው፡፡» (አል-አእራፍ፡ 29).

አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿هُوَ الْحَيُّ لَا إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ فَادْعُوهُ مُخْلِصِينَ لَهُ الدِّينَ ۗ الْحَمْدُ لِلَّهِ رَبِّ الْعَالَمِينَ﴾ [غافر: ٦٥]

“እርሱ ብቻ (ሁል ጊዜ) ሕያው ነው፤ ከርሱ ሌላ አምላክ የለም፤ ሃይማኖትንም ለርሱ ያጠራችሁ ስትኾኑ «ምስጋና ለዓለማት ጌታ ለአላህ ይኹን” የምትሉ ኾናችሁ ተገዙት፡” (ጋፊር፡ 65).

አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ادْعُوا رَبَّكُمْ تَضَرُّعًا وَخُفْيَةً ۚ إِنَّهُ لَا يُحِبُّ الْمُعْتَدِينَ ﴿٥٥﴾ وَلَا تُفْسِدُوا فِي الْأَرْضِ بَعْدَ إِصْلَاحِهَا وَادْعُوهُ خَوْفًا وَطَمَعًا ۚ إِنَّ رَحْمَتَ اللَّهِ قَرِيبٌ مِّنَ الْمُحْسِنِينَ﴾ [الأعراف: ٥٥-٥٦]

“ጌታችሁን ተዋርዳችሁ፣ በድብቅ ለምኑት፤እርሱ ወሰን ሀላፊዎችን አይወድምና፡፡ በምድር ውስጥ ከተበጀች በኋላ አታበላሹ፤ ፈርታችሁትና ከጅላችሁ ተገዙት፤ የአላህ ችሮታ ከበጎ አድራጊዎች ቅርብ ነውና፡፡” (አል-አዕራፍ፡ 55-56)

ኢማም አትርሚዚ በዘገቡት ሀዲስ አብዱላህ ቢን ዐባስ (ረዐ) እንዲህ ይላል፡ በጉዞ ላይ ከነብዩ (ሰዐወ) በኋላ ነበርኩኝ፣ እንዲህ አሉኝ፡

«يَا غُلامُ! إِنِّي مُعَلِّمُكَ كَلِمَاتٍ: احْفَظِ اللهَ يَحْفَظْكَ، احْفَظِ اللهَ تَجِدْهُ تُجَاهَكَ، وَإِذَا سَأَلْتَ فاَسْأَلِ اللهَ، وَإِذَا اسْتَعَنْتَ فَاسْتَعِنْ بِاللهِ، وَاعْلَمْ أَنَّ الْأُمَّةَ لَوِ اجْتَمَعُوا عَلَى أَنْ يَنْفَعُوكَ، لَمْ يَنْفَعُوكَ إِلا بِشَيْءٍ قَدْ كَتَبَهُ اللهُ لَكَ، وَلَوِ اجْتَمَعُوا عَلَى أَنْ يَضُرُّوكَ، لَمْ يَضُرُّوكَ إِلا بِشَيْءٍ قَدْ كَتَبَهُ اللهُ عَلَيْكَ، رُفِعَتِ الْأَقْلامُ، وَجَفَّتِ الصُّحُفُ».

‹አንተ ልጅ እኔ ቃላቶችን አስተምርሀለው፤ የአላህን ድምበር ጠብቅ፣ አላህ ይጠብቅሀልና፡፡ አላህን ጠብቅ አላህን ፊት ለፊትህ ታገኘዋለ፡፡ በምትለምንበት ጊዜ አላህን ለምን፡፡ እርዳታን ስት-ጠይቅ ከአላህ ጠይቅ፡፡ ሰዎች ሁሉ አንተን ለመጥቀም ቢሰባሰቡ አላህ በጻፈልህ ነገር እንጂ አይጠቅሙሁም፡፡ አንተን ለመጉዳት ቢሰበሰቡም አላህ ባንተ ላይ በጻፈ ነገር እንጂ አይጎዱሁም፡፡ መጻፊያዎምተነስታለች፤ ወረቀቷም ደርቃለች፡፡› ሰነዱ ጠንካራ ነው፤ ትርሚዚ ሀዲሱ ሀሰን ሰሒሕ ነው አለ፡፡

3

# አላህ በላቀ መጽሐፉ

ውስጥ ከአላህ ሌላ የለመነ ሰው ክህደትና ሽርክ ውስጥ እንደ ገባ ይገልጻል፡አላህ እንዲህ ይላል፡

﴿ وَمَن يَدۡعُ مَعَ ٱللَّهِ إِلَٰهًا ءَاخَرَ لَا بُرۡهَٰنَ لَهُۥ بِهِۦ فَإِنَّمَا حِسَابُهُۥ عِندَ رَبِّهِۦٓۚ إِنَّهُۥ لَا يُفۡلِحُ ٱلۡكَٰفِرُونَ ﴾ [المؤمنون: ١١٧]

‹ከአላህ ጋር ሌላን አምላክ፣ ለርሱ በርሱ ማስረጃ የሌለውን የሚገዛ ሰው፣ ምርመራው ጌታው ዘንድ ብቻ ነው፤ እነሆ ከሓዲዎች አይድኑም፡፡› (አል-ሙእሚኑን፡ 117)

ይህን የሰራ ሰው አንቀጹ ውስጥ እንደተጠቀሰዉ ከሓዲ ነው፡፡

አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَمَنۡ أَضَلُّ مِمَّن يَدۡعُواْ مِن دُونِ ٱللَّهِ مَن لَّا يَسۡتَجِيبُ لَهُۥٓ إِلَىٰ يَوۡمِ ٱلۡقِيَٰمَةِ وَهُمۡ عَن دُعَآئِهِمۡ غَٰفِلُونَ ٥ وَإِذَا حُشِرَ ٱلنَّاسُ كَانُواْ لَهُمۡ أَعۡدَآءٗ وَكَانُواْ بِعِبَادَتِهِمۡ كَٰفِرِينَ ﴾ [الأحقاف: ٥، ٦]

“እስከ ትንሣኤ ቀን ድረስ ለርሱ የማይመልስለትን ነገር ከአላህ ሌላ ከሚጠራ ሰው ይበልጥ የተሳሳተ ማነው? እነርሱም ከጥሪያቸው ዘንጊዎች ናቸው፡፡ ሰዎችም በተሰበሰቡ ጊዜ (ጣዖቶቹ) ለነርሱ ጠላቶች ይኾናሉ፤ (እነሱን) መገዛታቸውንም ከሓዲዎች ይኾናሉ፡፡› (አል-አሕቃፍ፡ 5-6).

ይህን ድርጊት፣ ከአላህ ሌላ መለመንን፣ ከፈጸመ ሰው የበለጠ በደለኛ የለም፡፡

አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿قُلۡ إِنَّمَآ أَدۡعُواْ رَبِّي وَلَآ أُشۡرِكُ بِهِۦٓ أَحَدٗا﴾ [الجن:٢٠]

«እኔ የምግገዛው ጌታዬን ብቻ ነው፤ በርሱም አንድንም አላጋራም› በል፡፡» (አልጅን፡ 20).

ይህ ማለት ከሱ ውጭ ያሉ ፍጡራንን በመለመን አላጋራም ነው፡፡

4

# አላህ (ሱ.ወ)

ሰዎች ደረጃቸው የፈለገ ያክል ቢከበርም አላህ ያስቻላቸው ነገር እንጂ ሌላን እንደ ማይችሉ ነገረን፡፡ ሁላቸውም ከአላህ ከጃይ ናቸው፡፡ እነሱ እንደኛው ሰዎች ናቸው፤ ሰውን የሚያገጥም ሁሉ እነሱንም ያጋጥማል፡፡ ይበላሉ፤ ይጠጣሉ፤ ይታመማሉ፤ ይሞታሉ፡፡

አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿يَٰٓأَيُّهَا ٱلنَّاسُ أَنتُمُ ٱلْفُقَرَآءُ إِلَى ٱللَّهِ ۖ وَٱللَّهُ هُوَ ٱلْغَنِىُّ ٱلْحَمِيدُ﴾ [فاطر: ١٥]

‹እናንተ ሰዎች ሆይ! እናንተ (ሁል ጊዜ) ወደ አላህ ከጃዮች ናችሁ፤ አላህም እርሱ ተብቃቂው ምስጉኑ ነው፡፡› (ፋጢር፡ 15)

አላህ ከሙሳ ሲነግረን እንዲህ ይላል፡

﴿فَقَالَ رَبِّ إِنِّى لِمَآ أَنزَلْتَ إِلَىَّ مِنْ خَيْرٍ فَقِيرٌ﴾ [القصص: ٢٤]

“ጌታዬ ሆይ! እኔ ከመልካም ነገር ወደኔ ለሚወርደው ፈላጊ ነኝ› አለ፡፡›› (አል-ቀሰስ፡ 24).

አላህ ከኢብራም ሲነግረንም እንዲህ ይላል፡

﴿وَإِذَا مَرِضْتُ فَهُوَ يَشْفِينِ﴾ [الشعراء: ٨٠]

“በታመምኩም ጊዜ እርሱ ያሽረኛል፡፡›› (አሽ-ሹዐራእ፡ 80).

ዒሣና እናቱ ምግብ ይበሉ እንደ ነበረ ነገረን፡

﴿مَّا ٱلۡمَسِيحُ ٱبۡنُ مَرۡيَمَ إِلَّا رَسُولٞ قَدۡ خَلَتۡ مِن قَبۡلِهِ ٱلرُّسُلُ وَأُمُّهُۥ صِدِّيقَةٞۖ كَانَا يَأۡكُلَانِ ٱلطَّعَامَۗ ٱنظُرۡ كَيۡفَ نُبَيِّنُ لَهُمُ ٱلۡأٓيَٰتِ ثُمَّ ٱنظُرۡ أَنَّىٰ يُؤۡفَكُونَ﴾ [المائدة: ٧٥]

“የመርየም ልጅ አልመሲሕ፣ ከበፊቱ መልእክተኞች በእርግጥ ያለፉ የሆነ መልእክተኛ እንጅ ሌላ አይደለም፡፡ እናቱም በጣም እውነተኛ ናት፡፡ ሁለቱም ምግብን የሚበሉ ነበሩ፤ አንቀጾችን ለነርሱ (ለከሓዲዎች) እንዴት እንደምናብራራ ተመልከት፤ ከዚያም (ከእውነት) እንዴት እነደ ሚመለሱ ተመልከት፡፡” (አል-ማኢዳህ፡ 75)

አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿قُلۡ فَمَن يَمۡلِكُ مِنَ ٱللَّهِ شَيۡـًٔا إِنۡ أَرَادَ أَن يُهۡلِكَ ٱلۡمَسِيحَ ٱبۡنَ مَرۡيَمَ وَأُمَّهُۥ وَمَن فِي ٱلۡأَرۡضِ جَمِيعٗاۗ﴾ [المائدة: ١٧]

‹የመርየምን ልጅ አልመሲሕን፣ እናቱንም፣ በምድር ያለንም ሁሉ ለማጥፋት ቢሻ፣ ከአላህ ማዳንን የሚችል ማነው?” (አል-ማኢዳህ፡ 17)

አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿وَمَآ أَرۡسَلۡنَا قَبۡلَكَ مِنَ ٱلۡمُرۡسَلِينَ إِلَّآ إِنَّهُمۡ لَيَأۡكُلُونَ ٱلطَّعَامَ وَيَمۡشُونَ فِي ٱلۡأَسۡوَاقِۗ﴾ [الفرقان: ٢٠]

“ከአንተ በፊት ከመልእክተኞች፣ እነሱ በእርግጥ ምግብን የሚበሉ፣ በገበያዎች የሚሄዱ ሆነው እንጅ አልላክንም፡፡› (አልፉርቃን፡ 20)

ስለነብዩ ሙሐመድ (ሰዐወ) አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿إِنَّكَ مَيِّتٞ وَإِنَّهُم مَّيِّتُونَ﴾ [الزمر: ٣٠]

‹አንተ ሟች ነህ፤ እነርሱም ሟቾች ናቸው፡፡› (አዝ-ዙመር፡ 30)

አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَلَا تَقُولَنَّ لِشَاْىْءٍ إِنِّي فَاعِلٌ ذَٰلِكَ غَدًا ﴿٢٣﴾ إِلَّآ أَن يَشَآءَ ٱللَّهُ ۚ وَٱذْكُر رَّبَّكَ إِذَا
نَسِيتَ وَقُلْ عَسَىٰٓ أَن يَهْدِيَنِ رَبِّى لِأَقْرَبَ مِنْ هَٰذَا رَشَدًا ﴾ [الكهف: ٢٣]

“ለማንኛውም ነገር ‹እኔ ይህንን ነገ ሰሪ ነኝ› አት በል፤ “አላህ ያሻ እንደ ሆነ (እሠራዋለሁ)’ ብትል እንጂ፡፡” (አልከህፍ፡ 23- 24)

አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ قُلْ إِنَّمَآ أَنَا۠ بَشَرٌ مِّثْلُكُمْ يُوحَىٰٓ إِلَىَّ أَنَّمَآ إِلَٰهُكُمْ إِلَٰهٌ وَٰحِدٌ ۖ فَمَن كَانَ يَرْجُوا۟ لِقَآءَ رَبِّهِۦ فَلْيَعْمَلْ عَمَلًا
صَٰلِحًا وَلَا يُشْرِكْ بِعِبَادَةِ رَبِّهِۦٓ أَحَدًۢا ﴾ [الكهف: ١١٠]

“እኔ አምላካችሁ አንድ አምላክ ብቻ ነው ማለት፣ ወደኔ የሚወረድልኝ አምሣያችሁ ሰው ብቻ ነኝ፤ የጌታውንም መገናኘት የሚፈልግ ሰው መልካም ስራን ይስራ፤ በጌታውም መገዛት አንድንም አያጋራ›› በላቸው፡፡” (አል-ከህፍ፡ 110)

እንዲያውም ከዚህ ጋር አያይዞ የተወሰኑ ነብያቶችን ህዝቦቻቸው እንደ ገደሏቸው አላህ ነገረን፡

﴿ أَفَكُلَّمَا جَآءَكُمْ رَسُولٌۢ بِمَا لَا تَهْوَىٰٓ أَنفُسُكُمُ ٱسْتَكْبَرْتُمْ فَفَرِيقًا كَذَّبْتُمْ وَفَرِيقًا
تَقْتُلُونَ ﴾ [البقرة: ٨٧]

“ነፍሶቻችሁ በማትወደው ነገር መልክተኛ በመጣላችሁ ቁጥር (ከመከተል) ትኮራላችሁን? ከፊሉን አስተባበላችሁ፤ከፊሉንም ትገድላላችሁ፡፡” (አልበቀራ፡ 87)

በመጨረሻ የሚንደርስበት ድምዳሜ፣ ዱዓን መለመን የሚቻለው አላህ ብቻ መሆኑን ነው፡፡ እሱ በሁሉም ነገር ቻይ የሆነ ጌታ፣ በመቻሉም ከፍጡራን የተለየበት ነገር ነውና፡፡

አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ إِنَّ ٱلَّذِينَ تَدۡعُونَ مِن دُونِ ٱللَّهِ عِبَادٌ أَمۡثَالُكُمۡۖ فَٱدۡعُوهُمۡ فَلۡيَسۡتَجِيبُواْ لَكُمۡ إِن كُنتُمۡ صَٰدِقِينَ ﴾ [الأعراف: ١٩٤]

“እነዚያ ከአላህ ሌላ የሚትገዟቸው ብጤዎቻችሁ ተገዢዎች ናቸው፡፡ እውነተኞችም እንደኾናችሁ ጥሩዋቸውና ለእናንተ ይመልሱላችሁ፤ (መመለስ ግን አይችሉም)፡፡” (አል-አዕራፍ፡ 194)

አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿يَٰٓأَيُّهَا ٱلنَّاسُ ضُرِبَ مَثَلٌ فَٱسۡتَمِعُواْ لَهُۥٓۚ إِنَّ ٱلَّذِينَ تَدۡعُونَ مِن دُونِ ٱللَّهِ لَن يَخۡلُقُواْ ذُبَابًا وَلَوِ ٱجۡتَمَعُواْ لَهُۥۖ وَإِن يَسۡلُبۡهُمُ ٱلذُّبَابُ شَيۡـٔٗا لَّا يَسۡتَنقِذُوهُ مِنۡهُۚ ضَعُفَ ٱلطَّالِبُ وَٱلۡمَطۡلُوبُ ﴾ [الحج: ٧٣]

“እናንተ ሰዎች ሆይ! አስደናቂ ምሳሌ ተገለጸላችሁ፡፡ ለእርሱም አድምጡት፡፡ እነዚያ ከአላህ ሌላ የምትግገዟቸው (ጣዖታት) ዝንብን ፈጽሞ አይፈጥሩም፡፡ እርሱን (ለመፍጠር) ቢሰበሰቡም እንኳን (አይችሉም)፡፡ አንዳችንም ነገር ዝንቡ ቢነጥቃቸው ከእርሱ አያስጥሉትም፡፡ ፈላጊውም ተፈላጊውም ደከሙ፡፡” (አል-ሐጅ፡ 73)

አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَٱلَّذِينَ يَقُولُونَ رَبَّنَا ٱصۡرِفۡ عَنَّا عَذَابَ جَهَنَّمَۖ إِنَّ عَذَابَهَا كَانَ غَرَامًا﴾ [الفرقان: ٦٥]

“(የአላህ ባሮች) እነዚያ ‘ጌታችን ሆይ! የገሀነምን ቅጣት ከእኛ ላይ መልስልን ቅጣቷ የማይለቅ ነውና’ የሚሉት ናቸው፡፡” (አልፉርቃን፡ 65)

5

# ነብያቶች፣

የተከበሩ መልእክተኞች፣ ደጋግ የአላህ ባሮችና መላኢካዎች በሁሉም ጉዳያቸውና ሁኔታቸው ውስጥ አላህን ብቻ እንደ ሚለምኑ አላህ ነገረን፤ እነሱን መከተል ደግሞ በሁሉም ሰው ላይ ግዴታ ነው፡፡

ዩኑስ በዓሳ ሆድ ውስጥ ሆኖ ያደረገውን ዱዓ አላህ ነገረን፡

﴿ وَذَا ٱلنُّونِ إِذ ذَّهَبَ مُغَٰضِبٗا فَظَنَّ أَن لَّن نَّقۡدِرَ عَلَيۡهِ فَنَادَىٰ فِي ٱلظُّلُمَٰتِ أَن لَّآ إِلَٰهَ إِلَّآ أَنتَ سُبۡحَٰنَكَ إِنِّي كُنتُ مِنَ ٱلظَّٰلِمِينَ ﴾ [الأنبياء: ٨٧، ٨٨]

‹የዓሳውንም ባለቤት ተቆጥቶ በኼደ ጊዜ (አስታውስ)፡፡ በእርሱም ላይ ፈጽሞ የማንፈርድበት መኾናችንን ጠረጠረ፡፡ (ዓሳም ዋጠው)፡፡ በጨለማዎችም ውስጥ ኾኖ ከአንተ በቀር ሌላ አምላክ የለም፡፡ ጥራት ይገባህ፡፡ እኔ በእርግጥ ከበዳዮቹ ነበርኩ በማለት ተጣራ፡፡ ለርሱም ጥሪውን ተቀበልነው፡፡ ከጭንቅም አዳነው፡፡ እንደዚሁም ምእመናንን እናድናለን፡፡› (አል-አምብያእ፡ 87-88)

አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَزَكَرِيَّآ إِذۡ نَادَىٰ رَبَّهُۥ رَبِّ لَا تَذَرۡنِي فَرۡدٗا وَأَنتَ خَيۡرُ ٱلۡوَٰرِثِينَ ٨٩ فَٱسۡتَجَبۡنَا لَهُۥ وَوَهَبۡنَا لَهُۥ يَحۡيَىٰ وَأَصۡلَحۡنَا لَهُۥ زَوۡجَهُۥٓۚ إِنَّهُمۡ كَانُواْ يُسَٰرِعُونَ فِي ٱلۡخَيۡرَٰتِ وَيَدۡعُونَنَا رَغَبٗا وَرَهَبٗاۖ وَكَانُواْ لَنَا خَٰشِعِينَ ﴾

[الأنبياء: ٨٩ – ٩٠]

“ዘከሪያንም ‘ጌታዬ ሆይ! ብቻዬን አትተወኝ፡፡ አንተም ከወራሾች ሁሉ በላጭ ነህ’ ሲል ጌታውን በተጣራ ጊዜ (አስታውስ)፡፡ ለእርሱም ጥሪውን ተቀበልነው፡፡ ለእርሱም የሕያን ሰጠነው፡፡ ለእርሱም ሚስቱን አበጀንለት፡፡ እነርሱ በበጎ ሥራዎች የሚቻኮሉ ከጃዮችና ፈሪዎች ኾነው የሚለምኑንም ነበሩ፡፡ ለእኛ ተዋራጆችም ነበሩ፡፡” (አል-አምብያእ፡ 89-90)

አላህ ከነቢ አዩብ ሲነግረን እንዲህ ይላል፡-

﴿۞وَأَيُّوبَ إِذۡ نَادَىٰ رَبَّهُۥٓ أَنِّي مَسَّنِيَ ٱلضُّرُّ وَأَنتَ أَرۡحَمُ ٱلرَّٰحِمِينَ ٨٣ فَٱسۡتَجَبۡنَا
لَهُۥ فَكَشَفۡنَا مَا بِهِۦ مِن ضُرّٖۖ وَءَاتَيۡنَٰهُ أَهۡلَهُۥ وَمِثۡلَهُم مَّعَهُمۡ رَحۡمَةٗ مِّنۡ عِندِنَا
وَذِكۡرَىٰ لِلۡعَٰبِدِينَ﴾ [الأنبياء: ٨٣، ٨٤]

“አዩብንም (ኢዮብን) ጌታውን «እኔ መከራ አገኘኝ አንተም ከአዛኞች ሁሉ ይበልጥ አዛኝ ነህ” ሲል በተጣራ ጊዜ (አስታውስ)፡፡ ለእርሱም ጥሪውን ተቀበልነው፡፡ ከጉዳትም በእርሱ ላይ የነበረውን ሁሉ አስወገድን፡፡ ቤተሰቦቹንም ከእነሱም ጋር መሰላቸውን ከእኛ ዘንድ ለችሮታና ለተገዢዎች ለማስገንዘብ ሰጠነው፡፡» (አል-አምብያእ፡ 83-84)

አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ٱلَّذِينَ يَحۡمِلُونَ ٱلۡعَرۡشَ وَمَنۡ حَوۡلَهُۥ يُسَبِّحُونَ بِحَمۡدِ رَبِّهِمۡ وَيُؤۡمِنُونَ بِهِۦ وَيَسۡتَغۡفِرُونَ لِلَّذِينَ
ءَامَنُواْ رَبَّنَا وَسِعۡتَ كُلَّ شَيۡءٖ رَّحۡمَةٗ وَعِلۡمٗا فَٱغۡفِرۡ لِلَّذِينَ تَابُواْ وَٱتَّبَعُواْ سَبِيلَكَ وَقِهِمۡ
عَذَابَ ٱلۡجَحِيمِ ٧ رَبَّنَا وَأَدۡخِلۡهُمۡ جَنَّٰتِ عَدۡنٍ ٱلَّتِي وَعَدتَّهُمۡ وَمَن صَلَحَ مِنۡ ءَابَآئِهِمۡ
وَأَزۡوَٰجِهِمۡ وَذُرِّيَّٰتِهِمۡۚ إِنَّكَ أَنتَ ٱلۡعَزِيزُ ٱلۡحَكِيمُ﴾ [غافر: ٧، ٨]

“እነዚያ ዐርሹን የሚሸከሙት እነዚያም በዙሪያው ያሉት በጌታቸው

ምስጋና ያወድሳሉ፡፡ በእርሱም ያምናሉ፡፡ «ጌታችን ሆይ! ነገሩን ሁሉ በእዝነትና በዕውቀት ከበሃል፡፡ ስለዚህ ለእነዚያ ለተጸጸቱት መንገድህንም ለተከተሉት ምሕረት አድርግላቸው፡፡ የእሳትንም ቅጣት ጠብቃቸው፡፡’ እያሉ ለእነዚያ ላመኑት ምሕረትን ይለምናሉ፡፡ «ጌታችን ሆይ! እነርሱንም፣ ከአባቶቻቸውና ከሚስቶቻቸውም፣ ከዝርዮቻቸውም፣ የበጀውን ሁሉ እነዚያን ቃል የገባህላቸውን የመኖሪያ ገነቶች አግባቸው፡፡ አንተ አሸናፊው ጥበበኛው አንተ ነህና፡፡” (ጋፊር፡ 7-8)

ሰሒሕ ውስጥ ከኢብን ዐባስ በተዘገበ ነብዩ (ሰዐወ) የበድር ዘመቻ ቀንእለት እንዲህ አሉ፡

«اللَّهُمَّ إِنِّي أَنْشُدُكَ عَهْدَكَ وَوَعْدَكَ، اللَّهُمَّ إِنْ شِئْتَ لَمْ تُعْبَدْ»

“ያ አላህ ሆይ! በቃል ኪዳንህና በቀጠሮህ እለምንሃለው፤ ከፈለክ ከዚህ ቡሃላ አትመለክም፡፡»

አቡ በክር እጃቸውን ያዘና ይበቃዎታል አላቸው፡፡ ከዚያም “ጭፍሮቹ ይበተናሉ፤ ወደ ኋላም ይሸሻሉ» እያሉ ወጡ፡፡

አልሓፊዝ በፈትሁል ባሪ ውስጥ እንዲህ ይላል፡ ኢማም አጥ-ጠብራኒ ዘንድ ሐሰን በሆነ ሰነድ ከኢብን መስዑድ በተዘገበው እንዲህ አለ፡ “ነብዩ ሙሐመድ የበድር ዘመቻ ቀን ጌታቸውን ከጠየቁት የበለጠ አንድም ጠያቂ የጠፋበትን ነገር ሲያጠያይቅ ሰምተን አናዉቅም፡ ‹ያ አላህ ሆይ! እኔ በቃል ኪዳኒህ እጠይቀሃለው› አሉ፡፡»

6

# ፍጥረተ-ዓለሙና

በውስጡ ያለው ሁሉ የአላህ ነው፤ በሱ ቁጥጥር ስርም ነው፤ የሱ ይዞታም ነው፡፡ ስለዚህ ሊለመን የሚገባዉ እሱ ብቻ ነው፤ ምክንያቱም ስልጣኑ የሱ ነው፤ፍጥረቱም የሱ ፍጥረት ብቻ ነው፤ ትእዛዝም የሱ ትእዛዝ ብቻ ነውና፡፡

አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ٱلرَّحۡمَٰنُ عَلَى ٱلۡعَرۡشِ ٱسۡتَوَىٰ ٥ لَهُۥ مَا فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَمَا فِي ٱلۡأَرۡضِ وَمَا بَيۡنَهُمَا وَمَا تَحۡتَ ٱلثَّرَىٰ﴾ [طه: ٥، ٦]

“አልረሕማን በዐርሹ ላይ (ለሱ በሚገባው መልኩ) ተደላደለ፡፡ በሰማያት ያለው፣ በምድርም ያለው፣ በመካከላቸውም ያለው፣ ከአፈር በታችም ያለው ሁሉ የርሱ ብቻ ነው፡፡›› (ጣሃ፡ 5-6).

አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿يَعۡلَمُ مَا يَلِجُ فِي ٱلۡأَرۡضِ وَمَا يَخۡرُجُ مِنۡهَا وَمَا يَنزِلُ مِنَ ٱلسَّمَآءِ وَمَا يَعۡرُجُ فِيهَاۖ وَهُوَ مَعَكُمۡ أَيۡنَ مَا كُنتُمۡۚ وَٱللَّهُ بِمَا تَعۡمَلُونَ بَصِيرٞ﴾ [الحديد: ٤]

“በምድር ውስጥ የሚገባውን፣ ከእርሷም የሚወጣውን፣ ከሰማይም የሚወርደውን በእርሷም ውስጥ የሚያርገውን ያውቃል፡፡ እርሱም የትም ብትኾኑ ከእናንተ ጋር ነው፡፡ አላህም የምትሠሩትን ሁሉ ተመልካች ነው፡፡›› (አልሐዲድ፡ 4).

አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿إِن تَدۡعُوهُمۡ لَا يَسۡمَعُواْ دُعَآءَكُمۡ وَلَوۡ سَمِعُواْ مَا ٱسۡتَجَابُواْ لَكُمۡۖ وَيَوۡمَ ٱلۡقِيَٰمَةِ يَكۡفُرُونَ بِشِرۡكِكُمۡۚ وَلَا يُنَبِّئُكَ مِثۡلُ خَبِيرٖ﴾ [فاطر: ١٤]

“ብትጠሩዋቸው ጥሪያችሁን አይሰሙም፡፡ ቢሰሙም ኖሮ ለእናንተ አይመልሱላችሁም፡፡ በትንሣኤም ቀን (እነርሱን በአላህ) ማጋራታችሁን ይክዳሉ፡፡ እንደ ውስጠ ዐዋቂው ማንም አይነግርህም፡፡›› (ፋጢር፡ 14)

አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ٱللَّهُ ٱلصَّمَدُ﴾ [الإخلاص: ٤]

“አላህ የሁሉ መጠጊያ ነው፡፡›› (አል-እኽላስ፡ 4).

አሰመድ ማለት ፍጡራን ጉዳያቸውን ለማስፈጸም ወደሱ የሚጠጉ ማለት ነው፡፡

7

# ነብያቶችና የተከበሩ

መልእክተኞች በተወሰነ ግዜ ለጉዳያቸው አላህን ለምነው እንዳልተቀበላቸውና ፍላጎታቸው እንዳልተሳካላቸው አላህ (ሱወ) ነገረን፡፡ አላህ ከነብዩ ሙሐመድ (ሰዐወ) እንዲህ ሲል ነገረን፡

﴿ إِنَّكَ لَا تَهْدِي مَنْ أَحْبَبْتَ وَلَٰكِنَّ اللَّهَ يَهْدِي مَن يَشَاءُ ۚ وَهُوَ أَعْلَمُ بِالْمُهْتَدِينَ ﴾

[القصص: ٥٦]

“አንተ የወደድከውን ሰው ፈጽሞ አታቀናም፡፡ ግን አላህ የሚሻውን ሰው ያቀናል እርሱም ቅኖቹን ዐዋቂ ነው፡፡›› (አል-ቀሠሥ፡ 56).

አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿اسْتَغْفِرْ لَهُمْ أَوْ لَا تَسْتَغْفِرْ لَهُمْ إِن تَسْتَغْفِرْ لَهُمْ سَبْعِينَ مَرَّةً فَلَن يَغْفِرَ اللَّهُ لَهُمْ ﴾

[التوبة: ٨٠]

“ለእነርሱ ምሕረትን ለምንላቸው፤ ወይም ለእነሱ ምሕረትን አትለምንላቸው (እኩል ነው)፡፡ ለእነሱ ሰባ ጊዜ ምሕረትን ብትለምንላቸው አላህ ለነሱ በፍጹም አይምርም፡፡ ይህ እነርሱ አላህና መልክተኛውን በመካዳቸው ነው፡፡ አላህም አመጸኞች ሕዝቦችን አያቀናም፡፡›› (አት-ተውባ፡ 80)

አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ مَا كَانَ لِلنَّبِيِّ وَالَّذِينَ آمَنُوا أَن يَسْتَغْفِرُوا لِلْمُشْرِكِينَ وَلَوْ كَانُوا أُولِي قُرْبَىٰ مِن بَعْدِ مَا تَبَيَّنَ لَهُمْ أَنَّهُمْ أَصْحَابُ الْجَحِيمِ ﴾ [التوبة: ١١٣]

“ለነቢዩና ለነዚያ ላመኑት ለአጋሪዎቹ የዝምድና ባለቤቶች ቢኾኑም እንኳ እነሱ (ከሓዲዎቹ) የእሳት ጓዶች መኾናቸው ከተገለጸላቸው በኋላ ምሕረትን ሊለምኑ የሚገባ አልነበረም፡፡›› (አት-ተውባ፡ 113)

ስለ ኢብራሂም ደግሞ አላህ እንዲህ ይላል፡

﴿ وَمَا كَانَ ٱسۡتِغۡفَارُ إِبۡرَٰهِيمَ لِأَبِيهِ إِلَّا عَن مَّوۡعِدَةٖ وَعَدَهَآ إِيَّاهُ فَلَمَّا تَبَيَّنَ لَهُۥٓ أَنَّهُۥ عَدُوّٞ لِّلَّهِ تَبَرَّأَ مِنۡهُۚ إِنَّ إِبۡرَٰهِيمَ لَأَوَّٰهٌ حَلِيمٞ ﴾ [التوبة: ١١٤]

“የኢብራሂምም ለአባቱ ምሕረትን መለመን ለእርሱ ገብቶለት ለነበረችው ቃል (ለመሙላት) እንጂ ለሌላ አልነበረም፡፡ እርሱም የአላህ ጠላት መኾኑ ለእርሱ በተገለጸለት ጊዜ ከርሱ ራቀ፤ (ተወው)፡፡ ኢብራሂም በእርግጥ በጣም ርኅሩኅ ታጋሽ ነውና፡፡›› (አት-ተውባ፡ 114)

አላህ (ሱወ) ይህን ዱዓውን አለ መቀበሉ ግልጽ ነው፡፡

ስለ ኑህ አላህ (ሱወ) እንዲህ ይላል፡

﴿ وَنَادَىٰ نُوحٞ رَّبَّهُۥ فَقَالَ رَبِّ إِنَّ ٱبۡنِي مِنۡ أَهۡلِي وَإِنَّ وَعۡدَكَ ٱلۡحَقُّ وَأَنتَ أَحۡكَمُ ٱلۡحَٰكِمِينَ ٤٥ قَالَ يَٰنُوحُ إِنَّهُۥ لَيۡسَ مِنۡ أَهۡلِكَۖ إِنَّهُۥ عَمَلٌ غَيۡرُ صَٰلِحٖۖ فَلَا تَسۡـَٔلۡنِ مَا لَيۡسَ لَكَ بِهِۦ عِلۡمٌۖ إِنِّيٓ أَعِظُكَ أَن تَكُونَ مِنَ ٱلۡجَٰهِلِينَ ٤٦ قَالَ رَبِّ إِنِّيٓ أَعُوذُ بِكَ أَنۡ أَسۡـَٔلَكَ مَا لَيۡسَ لِي بِهِۦ عِلۡمٞۖ وَإِلَّا تَغۡفِرۡ لِي وَتَرۡحَمۡنِيٓ أَكُن مِّنَ ٱلۡخَٰسِرِينَ ﴾ [هود: ٤٥-٤٧]

“ኑሕም ጌታውን ጠራ፡፡ አለም «ጌታዬ ሆይ! ልጄ ከቤተሰቤ ነው፡፡ ኪዳንህም እውነት ነው፡፡ አንተ ከፈራጆች ሁሉ ይበልጥ ዐዋቂ ነህ፡፡ (አላህም) «ኑሕ ሆይ! እርሱ ከቤተሰብህ አይደለም፤ እርሱ መልካም ያልሆነ ሥራ ነው፤ በርሱ ዕውቀት የሌለህንም ነገር አትጠይቀኝ፤ እኔ ከሚሳሳቱት ሰዎች እንዳትሆን እገስጽሀለሁ” አለ፡፡ «ጌታዬ ሆይ!

በእርሱ ለእኔ ዕውቀት የሌለኝን ነገር የምጠይቅህ ከመሆን እኔ ባንተ እጠበቃለሁ፡፡ ለእኔም ባትምረኝና ባታዝንልኝ ከከሳሪዎቹ እሆናለሁ” አለ፡፡›› (ሁድ፡ 45-47) ታዲያ ከአላህ በታች እነሱን እንዴት ይለምናሉ?

አሁንም በድጋሜ እንመልከት፤ የኡሁድ ዘመቻ ቀን ሙስሊሞች በአላህ መልእክተኛ (ሰዐወ) መሪነት ሙሽሪኮችን በተዋጉ ግዜ በነሱ ላይ ድል ማግኘትን ይፈልጉ ነበር፡፡ ነገር ግን አስፈላጊዉን እንቅስቃሴ ሁሉ ከማድረጋቸዉም ጋር አልተሳካላቸውም፡፡ በዚህም ምክንያት አላህ በአሊ-ዒምራን ምእራፍ ውስጥ ብዙ ግሳጼን የያዙ እና ለሙስሊሞች አስተማሪ የሆኑ አንቀጾችን አወረደ፡፡

የስፊን ዘመቻ ቀን በዐሊ ቢን አቡ ጣሊብ ላይ የተከሰተውንም እንመልከት፤ በተቃራኒው ላይ ድል ለማግኘት ሞክሮ የቻለውን ታግሎ ነበር፡፡ ግን ፍላጎቱ አልተሳካለትም፡፡

ሑሴንንም (ረዐ) እንመልከት፡ እሱና ከሱ ጋር የነበሩ ብዙ ቤተ ሰቦቹ እስኪገደሉ ድረስ ታግለው ተዋግተው ነበሩ፡፡ ነገር ግን ከራሱም ሆነ ከቤተሰቦቹ ምንም ነገር መከላከል አልቻለም፡፡

ታድያ እነዚያ አላህን ትተው ዐሊንና ሑሴንን የሚለምኑ የት ነው ያሉት? ከራሳቸውም መከላከል አልቻሉም፤ በነሱና በቤተሰቦቻቸው የተላለፈውን የአላህን ቀደር መመለስም አልቻሉም፡፡ ይህ ጉዳይ(የአላህን ቀደር መመለስ አለመቻል)ግልጽ እና በማንምጤናማ አእምሮም ባለዉ ሰዉየ ሚታወቅ ነገር ነው፤ አንድም ሰው ከሱ ሊያመልጥ አይችልም፡፡ ተጨባጭ ጉዳይም ስለሆነ መካዱ አይመችም፡፡ ዐሊና ሑሴን በችግር ጊዜ ወደአላህ ይመለሱና እሱን ይለምኑ ነበር፡፡ እነሱን ወዳለው የሚል ሰው ሁሉ ላይ እነሱን መከተል ግዴታ ይሆናል፡፡

የተወሰኑ ሰዎች ድምበር አለፉና በአላህ ቤት ውስጥ ከዕባ ዘንድ እያሉ ራሱ፣ መቆም ሲፈልጉ ‹ያ ዐሊ!› ይላሉ፡፡ የሆነ አዋቂ ሰምቶት እንዲህ አለው፡- “በአንድ ሰው ቤት ውስጥ ብትሆንና ከቤቱ ውስጥ የሆነ ነገር ብትፈልግ፣ ለጉዳዩ ወደ ቤቱ ጎሮቤት ነው ምትሄደው ወይስ ባለ ቤቱን ራሱ ነው ምትጠይቀው?›› አለው፡፡ ሰውየውም ሌላ መልስ አጣና ባለ ቤቱውን ነው ምጠይቀው አለ፡፡

ለዚህ ሲል አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ أُولَٰٓئِكَ ٱلَّذِينَ يَدۡعُونَ يَبۡتَغُونَ إِلَىٰ رَبِّهِمُ ٱلۡوَسِيلَةَ أَيُّهُمۡ أَقۡرَبُ وَيَرۡجُونَ رَحۡمَتَهُۥ وَيَخَافُونَ عَذَابَهُۥٓۚ إِنَّ عَذَابَ رَبِّكَ كَانَ مَحۡذُورٗا ﴾ [الإسراء: ٥٧]

“እነዚያ እነርሱ የሚግገዟቸው ማንኛቸውም (ወደ አላህ) በጣም ቀራቢያቸው ወደ ጌታቸው መቃረቢያን (ሥራ) ይፈልጋሉ፡፡ እዝነቱንም ይከጅላሉ፡፡ ቅጣቱንም ይፈራሉ፡፡ የጌታህ ቅጣት የሚፈራ ነውና፡፡›› (አል-ኢስራእ፡ 57)

ሁሉም ሰው የሚገነዘበውን ሌላ ምሳሌን አብራላለው፡ አንድን ሰው በንብረት አላህ አብቃቃው፤ ብዙ ገንዘብን ሰጠው፡፡ ብዙ ልጆችም ነበሩት፡፡ ሁሌም ለልጆቹ ገንዘብ፣ ምግብ ወይም ልብስ ስትፈልጉ ንገሩኝ ይል ነበር፡፡ እነኚህ ልጆች እሱን አይጠይቁም፤ ወደ ጎረቤት ሂደው እነሱን ይጠይቁ ነበር፡፡ ልጆቹ የሰሩት ስራ ከአእምሮ ጋር የሚሄድ ነውን ወይስ አእምሮን የሚጋጭ ቂልነት ነው? ይሄ በፍጡራን ጋር የተያያዘ ጉዳይ ነው፡፡ የላቀ ባህርያት ያለው አላህ ጋር የተያያዘ ጉዳይስ እንዴት ይሁን?

ሁሉም ባሮች ጉዳያቸውን ለማስፈጸም እና ችግሮቻቸውን ለመፍታት፣ ፈጣርያቸውና አምላካቸው ወደ ሆነው ወደ አላህ መመለስ አለበት፡፡

የተወሰኑ ሰዎች ከአላህ ሌላ ነቢያቶችን ለመለመን የነሱን ተዓምር ለመስረጃነት ያቀርባሉ፡- ለምሳሌ ሙሣ በብትራቸው ድንጋይን ሲመቱ ውሃ ይፈልቅ ነበር፤ ዒሳ ደግሞ ሙታንን ይቀሰቅስ ነበር፤ እውራንና ለምጻኛን ያድን ነበር፡፡

ለዚህ ጥያቂ መልስ የሚከተለውን አቀርባለው፡-

- **1**ኛ፡- እነዚህ ተዓምራቶች ከአላህ የተሰጣቸው ናቸው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿وَرَسُولًا إِلَىٰ بَنِي إِسْرَائِيلَ أَنِّي قَدْ جِئْتُكُم بِآيَةٍ مِّن رَّبِّكُمْ ۖ أَنِّي أَخْلُقُ لَكُم مِّنَ الطِّينِ كَهَيْئَةِ الطَّيْرِ فَأَنفُخُ فِيهِ فَيَكُونُ طَيْرًا بِإِذْنِ اللَّهِ ۖ وَأُبْرِئُ الْأَكْمَهَ وَالْأَبْرَصَ وَأُحْيِي الْمَوْتَىٰ بِإِذْنِ اللَّهِ﴾ [آل عمران: ٤٩].

«እኔ ከጌታዬ ዘንድ በተዓምር ወደ እናንተ መጣሁ፡፡ እኔ ለናንተ ከጭቃ እንደ ወፍ ቅርፅ እፈጥራለሁ፡፡ በርሱም እተነፍስበታለሁ፡፡ በአላህም ፈቃድ ወፍ ይኾናል፡፡ በአላህም ፈቃድ ዕውር ኾኖ የተወለደን፣ ለምጻኛንም አድናለሁ፡፡ ሙታንንም አስነሳለሁ፡፡ የምትበሉትንና በቤታችሁ የምታደልቡትንም ሁሉ እነግራችኋለሁ፡፡ የምታምኑ እንደኾናችሁ ለእናንተ በዚህ ውስጥ በእርግጥ ተዓምር አለበት፡፡” (ኣሊ. ዒምራን፡ 49)

በባርያ ላይ ያለው ግዴታ እነዚህን ተዓምራት የሰጣቸውን አላህን ብቻ መለመን ነው፡፡

- **2**ኛ፡- በብዙ አንቀጾች ውሰጥ እንዳሳለፍነው፣ እነዚህ ነቢያቶች አላህን ይለምኑ ነበሩ፡፡ ሰው ሁሉ እነሱን መከተል አለበት፤ እነሱ ጥሩ አርዓያ ናቸውና፡፡

**3ኛ፡-** ያለፉት መረጃዎች ከዚህ በመካልከል ግልጽ አስረጅዎች ናቸው፡፡ እንደውም የሰው ልጅ በሚችለው ጉዳይ ላይ ራሱ አስቀድሞ በአላህ መጀመር ይመረጣል፡፡

ከአቢ ጀዕፈረ ሙሐመድ አልባቂር እነደተዘገበ እንዲህ ይላል፡- “ወደ ፍጡራን የሚወስደው ጉዳይ ያጋጠመው ሰው በአላህ (ሱወ) ይጀምር፡፡››[1]

1- ኪታብ ‹አልሙሰተጊሲን ቢላህ› የኢብን በሽክዋል 68 ገጽ

# 8

# አላህ (ሱወ) እሱን ብቻ

መለመን እንዳዘዘና ከሱ ሌላን መለመን እንደ ከለከለ፣ ባሮቹ በሁሉም ጉዳያቸው አሱን መለመን፣ ከሱ እርዳታን መፈለግና ወደሱ መመለስን ይወዳል፡፡ ዱዓ አለህ የሚወደው ዒባዳ ነው፤ ጌታውን የሚለምን ሰው እሱ የሚወደውንና ወደሱ የሚያቃርብ ነገርን እየሰራ ነው፡፡ የዚህ መረጃ ሐዲስ አልቁድሲ ነው፤ እሱ ታላቅ ሐዲስ ሲሆን የአላህ መልእክተኛ እንዲህ አሉ፡-

«يَنْزِلُ رَبُّنَا تَبَارَكَ وَتَعَالَى كُلَّ لَيْلَةٍ إِلَى السَّمَاءِ الدُّنْيَا حِينَ يَبْقَى ثُلُثُ اللَّيْلِ الآخِرُ يَقُولُ: مَنْ يَدْعُونِي، فَأَسْتَجِيبَ لَهُ مَنْ يَسْأَلُنِي فَأُعْطِيَهُ، مَنْ يَسْتَغْفِرُنِي فَأَغْفِرَ لَهُ»

"ጌታችን በሁሉም ሌሊት ወደ ቅርቢቷ አለም ሰማይ ይወርዳል፤ ‹ለምኖኝ የሚመልስለት ማነው? ጠይቆኝ የሚሰጠው ማነው? ምህረት ጠይቆውኝ የሚምረው ማነው?› ይላል፡፡››

ይህ ሐዲስ ከብዙ ሠሓቦች ተዘግቧል፡፡ ይህ ሐዲስ በሠሒሐይን፣ ሱነንና ሙስነዶች ውስጥ የሚገኝ ሲሆን ሙተዋትር (በብዙ አቅጣጫ የተዘገበ) ሐዲስ ነው፤ ኢማም አድ-ዳረቁጥኒ እሱን ብቻ አስመልክቶ አንድ መጽሐፍ አለው፡፡

የአላህን ችሮታ ተመልከት፤ በሁሉም ሌሊት ባሮቹ እሱን እንዲ ጠይቁና እንዲ ለምኑት ይጠራቸዋል፡፡ እሱ ከነሱ የተብቃቃ ነው፡፡ባርያ ይህን

ታላቅ የአላህን ቸርነት ተጠቅሞ ዱዓውን ማብዛት አለበት፡፡ የልቡን መረጋጋት፣ የነፍሱን ማረፍና የኢማኑን መጨመር በቀላሉ ያገኛል፡፡

አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿وَسۡـَٔلُواْ ٱللَّهَ مِن فَضۡلِهِۦٓۚ إِنَّ ٱللَّهَ كَانَ بِكُلِّ شَيۡءٍ عَلِيمٗا﴾ [النساء: ٣٢]

“አላህንም ከችሮታው ለምኑት፡፡ አላህ በነገሩ ሁሉ ዐዋቂ ነው፡፡›› (አን-ኒሳእ፡ 32)

አቡ ዘር አል-ግፋሪ (ረዐ) እንዳስተላለፉት ነብዩ (ሰዐወ) ከጌታቸው በዘገቡልን አላህ እንዲህ አለ፡-

«يَا عِبَادِي إِنِّي حَرَّمْتُ الظُّلْمَ عَلَى نَفْسِي، وَجَعَلْتُهُ بَيْنَكُمْ مُحَرَّمًا، فَلَا تَظَالَمُوا، يَا عِبَادِي كُلُّكُمْ ضَالٌّ إِلَّا مَنْ هَدَيْتُهُ، فَاسْتَهْدُونِي أَهْدِكُمْ، يَا عِبَادِي كُلُّكُمْ جَائِعٌ، إِلَّا مَنْ أَطْعَمْتُهُ، فَاسْتَطْعِمُونِي أُطْعِمْكُمْ، يَا عِبَادِي كُلُّكُمْ عَارٍ، إِلَّا مَنْ كَسَوْتُهُ، فَاسْتَكْسُونِي أَكْسُكُمْ...».

“ባሮቼ ሆይ! እኔ በደልን በራሴ ላይ እርም አድርግያለው፤ በናንተመካከልም እርም አደረኩኝ፤ ስለዚህ አትበዳደሉ፡፡ ‹ባሮቼ ሆይ! ሁላችሁም ጠማሞች ናችሁ እኔ የመራሁት ሲቀር፤ መመራትን ከኔ ለምኑ እመራችዋለው፡፡ ‹ባሮቼ ሆይ! ሁላችሁም ረሃብተኞች ናችሁ እኔ ያበላሁት ሲቀር፤ ምግብን ከኔ ፈልጉ እመግባችዋለው፡፡ ባሮቼ ሆይ! ሁላችሁም ራቁት ናችሁ ያለበስኩት ሲቀር፤ ልብስን ከኔ ጠይቁ ኣለብሳችዋለው፡፡›› (ሙስሊም ዘግቦታል)

አቡ ሁረይራ (ረዐ) እንዳስተላለፉት የአላህ መልእክተኛ (ሰዐወ) እንዲህ ብለዋል፡- “አላህን ያል-ለመነ ሰው አላህ ይቆጣበታል፡፡›› ኢብን ማጃህ ዘግበውታል፡፡ ይህን ሐዲስ የተወሰኑ ሊቃወንቶች አጠንክረዉታል፤

ሐዲሱ ዶዒፍ (ደካማ) ነው፡፡ ግን የቁርኣንና ሐዲስ ማስረጃ ለትርጉሙ ይመሰክራሉ፡፡ በጉዳዩ ሁሉ አላህን የማይለምን ሰው አላህ እንደ ሚቆጣበት ግልጽ ነው፡፡ አላህን ጌታም ሆኔ አምላክ አላደረገምና፡፡ ከዱዓዎች ዉስጥ ግዴታ የሚሆኑት አሉ፤ ለምሳሌ መመራትን አላህን መጠየቅ፣ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿ ٱهۡدِنَا ٱلصِّرَٰطَ ٱلۡمُسۡتَقِيمَ ﴾ [الفاتحة: ٦]

“ወደ ቀጥተኛ ጎዳና ምራን፡፡›› (አልፋትሓ፡ 6) በሁለቱ ሱጁድ መካከል እንዳለው ምህረት አላህን መጠየቅ አይነት፡፡

በአረብኛ ግጥም ውስጥ ‹አላህ ልመናውን ከተውከ ይቆጣል፤ የኣደም ልጅ ደግሞ ሲለመን ይቆጣል› ይላል፡፡

# 9

# ከቁርኣንና ሐዲስ

የሆኑ ሸሪዓዊ መስረጃዎች አላህ ብቻ በሚችለው ጉዳይ ላይ ከሱ ሌላ መለመን ክልክል መሆኑን እንዳመላከቱ ሁሉ የሰው ተፈጥሮም ይህንኑ ያመላክታል፡፡ አላህ (ሱ.ወ) የሰው ልጅን በችግርና አደጋ ግዜ ወደሱ በመመለስና እሱን በመለመን ላይ ነው የፈጠረው፡፡ ይሄ ከሃዲዎችንም ጨምሮ በሁሉም ሰው ውስጥ ይገኛል፡፡ አላህ ከሙሽሪኮች ነግሮን እንዲህ ይላል፡-

﴿هُوَ ٱلَّذِى يُسَيِّرُكُمْ فِى ٱلْبَرِّ وَٱلْبَحْرِ حَتَّىٰٓ إِذَا كُنتُمْ فِى ٱلْفُلْكِ وَجَرَيْنَ بِهِم بِرِيحٍ طَيِّبَةٍ وَفَرِحُوا۟ بِهَا جَآءَتْهَا رِيحٌ عَاصِفٌ وَجَآءَهُمُ ٱلْمَوْجُ مِن كُلِّ مَكَانٍ وَظَنُّوٓا۟ أَنَّهُمْ أُحِيطَ بِهِمْ دَعَوُا۟ ٱللَّهَ مُخْلِصِينَ لَهُ ٱلدِّينَ لَئِنْ أَنجَيْتَنَا مِنْ هَٰذِهِۦ لَنَكُونَنَّ مِنَ ٱلشَّٰكِرِينَ﴾ [يونس: ٢٢]

“እርሱ (አላህ) ያ በየብስና በባሕር የሚያስኬዳችሁ ነው፡፡ በመርከቦችም ውስጥ በሆናችሁና በእነርሱም በመልካም ነፋስ በርሷ የተደሰቱ ኾነው (መርከቦቹ) በተንሻለሉ ጊዜ ኀይለኛ ነፋስ ትመጣባታለች፡፡ ከየስፍራውም ማዕበል ይመጣባቸዋል፡፡ እነሱም (ለጥፋት) የተከበቡ መሆናቸውን ያረጋግጣሉ፡፡ (ያን ጊዜ) አላህን ከዚህች (ጭንቀት) ብታድነን በእርግጥ ከአመስጋኞቹ እንሆናለን ሲሉ ሃይማኖትን ለርሱ ብቻ ያጠሩ ሆነው ይለምኑታል፡፡›› (ዩኑስ፡ 22)

አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿وَإِذَا مَسَّكُمُ ٱلضُّرُّ فِي ٱلْبَحْرِ ضَلَّ مَن تَدْعُونَ إِلَّآ إِيَّاهُ فَلَمَّا نَجَّىٰكُمْ إِلَى ٱلْبَرِّ أَعْرَضْتُمْ وَكَانَ ٱلْإِنسَٰنُ كَفُورًا﴾ [الإسراء: ٦٧]

“በባሕሩም ውስጥ ጉዳት ባገኛችሁ ጊዜ የምትጠሩዋቸው (አማልክት) ሁሉ ከእርሱ (ከአላህ) በቀር ይጠፋሉ፡፡ ወደ የብስም በማድረስ ባዳናችሁ ጊዜ (እምነትን) ትተዋላችሁ፡፡ ሰውም በጣም ከሓዲ ነው፡፡» (አል-ኢስራእ፡ 67)

እንዲያውም እንሰሳዎችም ወደ ፈጣሪያቸው በመመለስ ላይ ነው የተፈጠሩት፤ አላህ (ሱ.ወ) ከሡለይማን እርግብ ሲነግረን እንዲህ ይላል፡-

﴿فَمَكَثَ غَيْرَ بَعِيدٍ فَقَالَ أَحَطتُ بِمَا لَمْ تُحِطْ بِهِۦ وَجِئْتُكَ مِن سَبَإٍۭ بِنَبَإٍ يَقِينٍ ﴿٢٢﴾ إِنِّي وَجَدتُّ ٱمْرَأَةً تَمْلِكُهُمْ وَأُوتِيَتْ مِن كُلِّ شَيْءٍ وَلَهَا عَرْشٌ عَظِيمٌ ﴿٢٣﴾ وَجَدتُّهَا وَقَوْمَهَا يَسْجُدُونَ لِلشَّمْسِ مِن دُونِ ٱللَّهِ وَزَيَّنَ لَهُمُ ٱلشَّيْطَٰنُ أَعْمَٰلَهُمْ فَصَدَّهُمْ عَنِ ٱلسَّبِيلِ فَهُمْ لَا يَهْتَدُونَ﴾ [النمل: ٢٢-٢٤]

“(ወፉ) ዕሩቅ ያልኾነንም ጊዜ ቆዬ፡፡ አለም «ያላወቅከውን ነገር አወቅኩ፡፡ ከሰበእም እርግጠኛን ወሬ አመጣሁልህ፡፡ «እኔ የምትገዛቸው የኾነችን ሴት ከነገሩም ሁሉ የተሰጠችን አገኘሁ፡፡ ለእርሷም ታላቅ ዙፋን አልላት፡፡ «እርስዋንም ሕዝቦችዋንም ከአላህ ሌላ ለፀሐይ ሲሰግዱ አገኘኋቸው፡፡ ሰይጣንም ለእነሱ ሥራዎቻቸውን ሸልሞላቸዋል፡፡ ከእውነተኛውም መንገድ አግዷቸዋል፡፡ ስለዚህ እነሱ (ወደ እውነት) አይምመሩም፡፡” (አን-ነምል፡ 22-24)

ይህ ወፍ አላህን ትተው ወደ ፍጡራን የተመለሱ ሰዎችን ስራ እንዴት እንደ ተቃወመ ተመልከት! ምክንያቱም ይህ ፍጥረት አላህ ፍጡራንን ባጠቃላይ ሰውን፣ ጅንን፣ ተናጋሪዎችንና የማይናገሩትንም የፈጠረበት ባህሪ ነውና፡፡

10

# ሸሪዓና ፍጥረት

ሸሪዓና ፍጥረት በዚህ ላይ እንዳመላከቱ ሁሉ ትክክለኛ አእምሮም ይህንኑ ይደግፋል፡፡ አእምሮ ያለው ሰው እነዚህ የሚመለኩ ነገራቶች በፍጥረታቸውና ሰውነታቸው የሱ አምሳያ መሆናቸውን ያውቃል፡፡ ታዲያ እንዴት ከአላህ ሌላ እነሱን እርዳታ ይጠይቃል? አምሳያዎቹ ሆኖስ እያሉ እንዴት ወደነሱ ተጠግቶ ማዳንና ሲሳይን ይለምናቸዋል?

አላህ (ሱ.ወ) ከነቢዩ ሲነግረን እንዲህ ይላል፡-

﴿قُلْ إِنَّمَآ أَنَا۠ بَشَرٌ مِّثْلُكُمْ يُوحَىٰٓ إِلَيَّ أَنَّمَآ إِلَٰهُكُمْ إِلَٰهٌ وَٰحِدٌ فَمَن كَانَ يَرْجُواْ لِقَآءَ رَبِّهِۦ فَلْيَعْمَلْ عَمَلًا صَٰلِحًا وَلَا يُشْرِكْ بِعِبَادَةِ رَبِّهِۦٓ أَحَدًۢا﴾ [الكهف: ١١٠]

«እኔ አምላካችሁ አንድ አምላክ ብቻ ነው ማለት ወደኔ የሚወረድልኝ ቢጤያችሁ ሰው ብቻ ነኝ፡፡ የጌታውንም መገናኘት የሚፈልግ ሰው፤ መልካም ሥራን ይሥራ፡፡ በጌታውም መገዛት አንድንም አያጋራ" በላቸው፡፡» (አልከህፍ፡ 110)

አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿قَالَتْ لَهُمْ رُسُلُهُمْ إِن نَّحْنُ إِلَّا بَشَرٌ مِّثْلُكُمْ وَلَٰكِنَّ ٱللَّهَ يَمُنُّ عَلَىٰ مَن يَشَآءُ مِنْ عِبَادِهِۦ ۖ وَمَا كَانَ لَنَآ أَن نَّأْتِيَكُم بِسُلْطَٰنٍ إِلَّا بِإِذْنِ ٱللَّهِ ۚ وَعَلَى ٱللَّهِ فَلْيَتَوَكَّلِ ٱلْمُؤْمِنُونَ﴾ [إبراهيم: ١١]

"መልክተኞቻቸው ለእነርሱ አሉ «እኛ ብጤያችሁ ሰው እንጂ ሌላ

አይደለንም ግን አላህ ከባሮቹ በሚሻው ሰው ላይ ይለግሳል፡፡ ለእኛም በአላህ ፈቃድ እንጂ ማስረጃን ልናመጣላችሁ አይገባንም፡፡ በአላህም ላይ ምእምናኖች ይጠጉ፡፡ (አል-ኢብራሂም፡ 11)

ባሳለፍነው አንቀጽ ውስጥ እንዲህ ይላል፡-

﴿ إِنَّ ٱلَّذِينَ تَدۡعُونَ مِن دُونِ ٱللَّهِ عِبَادٌ أَمۡثَالُكُمۡۖ فَٱدۡعُوهُمۡ فَلۡيَسۡتَجِيبُواْ لَكُمۡ إِن كُنتُمۡ صَٰدِقِينَ ﴾[الأعراف: ١٩٤]

“እነዚያ ከአላህ ሌላ የምትገዟቸው ብጤዎቻችሁ ተገዢዎች ናቸው፡፡›› (አል-አዕራፍ፡ 194)

እንዲያውም ባሮች መተግበር የሚችሉት ጉዳይ ቢሆኒም አላህን መለመንና ወደ ባሮች መዞር ማቆም ያስፈልጋል፡፡ የሚያሳዝነው ነገር ግን ሰዎች ሲታመሙ ወዲያው ሩቃ (ሸሪዓዊ ህክምና) ወደ ሚቀራ ሰው ይሄዳሉ፤ ከሱ የሚጠበቀው መጀመርያ በራሱ ላይ መቅራት ነበረበት፡፡ ከሙስሊሞች ውስጥ በራሱ ላይ ሱረት አል-ፋትሓ፣ ኣየት አልኩርሲይ፣ ሙዐወዘተይንና የመሳሰሉትን መቅራት የማይችል የለም፡፡

አንድ ሰው እራሱን በራሱ ሩቃ የሚያደርግ ከሆነ የበለጠ ትግል ማድረጉ ግልጽ ነው፡፡ የሚቀራውም ነገር ከልብ የመነጨና ከአላህ ጋር ጠንካራ ግንኙነት ያለው ይሆናል፡፡ ይህ ነው የበለጠ ተቀባይነት ማግኘቱ የሚከጀለው፡፡ እራሱን በራሱ ሩቃ አድርጎ አላህ ያዳነው ሰው ብዙ ነው፡፡

ሌላ ከዚው ጋር የተያያዘ ነጥብ ደግሞ የተወሰኑ ሰዎች ስራ ሲፈልጉ ወዲያው የሚያገናኛቸውን ሰው መፈለግ ይጀምራሉ፡፡ አላህ እንዲያገራለት ወደሱ ሳይመለስ እገሌንና እገሌን ማናገር ይጀምራል፡፡ አንድ ከቁርኣን

ማሰራጫ ጣብያ የሰማውትን ታሪክ አስታውሳለው፡- አንድ ሰው ስራን ፈለገና ጉዳዩ ወደ ሚመለከተው ሰው ሄደ፤ ዞረዉም አላዩትም፡፡ በጣም አዝኖ ወደ አንድ አሊም ሄዶ ምልጃን ጠየቀው፡፡ አሊሙም ወደ አላህ እንዲመለስ መከረው፤ የሱን ምክር ተቀብሎከሱብሒ ሰላት በፊት ተነስቶ ሰግዶ ዱዓ አደረገ፡፡ ከዚያ በኋላ መጀመርያ ወደ ሄደባቸው ሰዎች ሄደ፡፡ ስራውን ማግኘትም ቀለለለት፡፡ እንደውም ከዚያ በፊት ሄዶበት የነበረው ሰዉ ‹የት ነበርክ?› ብሎ ጠየቀው፡፡

አንድ አንድ ሰዎች ለራሳቸው ዱዓ ማድረግ ሲፈልጉ ሌሎች ሰዎች እንድያደርጉላቸው ይጠይቃሉ፤ ጌታችን እንዲህ ይላል፡-

﴿وَقَالَ رَبُّكُمُ ٱدۡعُونِيٓ أَسۡتَجِبۡ لَكُمۡۚ﴾ [غافر: ٦]

“ጌታችሁም አለ «ለምኑኝ፤ እቀበላችኋለሁና፡፡ እነዚያ እኔን ከመግገዛት የሚኮሩት ተዋራጆች ኾነው ገሀነምን በእርግጥ ይገባሉ፡፡›› (ጋፊር፡ 60)

አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿وَإِذَا سَأَلَكَ عِبَادِي عَنِّي فَإِنِّي قَرِيبٌۖ أُجِيبُ دَعۡوَةَ ٱلدَّاعِ إِذَا دَعَانِۖ فَلۡيَسۡتَجِيبُواْ لِي وَلۡيُؤۡمِنُواْ بِي لَعَلَّهُمۡ يَرۡشُدُونَ﴾ [البقرة: ١٨٦]

“ባሮቼም ከእኔ በጠየቁህ ጊዜ (እንዲህ በላቸው)፡- እኔ ቅርብ ነኝ፡፡ የለማኝን ጸሎት በለመነኝ ጊዜ እቀበለዋለሁ፡፡ ስለዚህ ለኔ ይታዘዙ፤ በኔም ይመኑ፤ እነሱ ሊመሩ ይከጀላልና፡፡›› (አልበቀራ፡ 186)

አንድ አሥበግ ቢን ዘይድ አልወራቅ የሚባል ሰለፍ እንዲህ ይላል፡- “እኔና ከኔ ጋር የቆዩ ሰዎች ለሶስት ቀን ምንም ሳንበላ ቆየን፡፡ ወደ ታናሽ ሴት ልጄ ወጣሁኝ፤ ‹አባቴ ርቦኛል› አለች፡፡ እሷን ትቼ የዉዱ ቦታ ሄድኩኝ፤ ዉዱ አድርጌ ሁለት ረከዓ ሰገድኩ፡፡ ዱዓ ለማድረግ

እጆቼን ስዘረጋ ከዚህ በፊት የማውቀው ዱዓ ሁሉ ጠፋብኝ፡፡”ያ አላህ ሆይ! ሲሳይን ብትከለክለኝም ዱዓን ግን አትከልክለኝ›› አልኩኝ፡፡ ቀጥሎ ያለው ዱዓ መጣልኝ፡-

«اللهم خشعت الأصوات لك، وضلت الأحلام فيك، وضاقت الأشياء دونك، وهرب كل شيء منك إليك، وتوكل كل مؤمن عليك، فأنت الرفيع في جلالك، وأنت البهي في جمالك، وأنت العلي في قدرك، يا من هو في علوه دان، وفي دونه عال، وفي سلطانه قوي صل على محمد وعلى آل محمد وافتح عليّ منك رزق، لا تجعل عليّ فيه منّة، ولا لك علي فيه في الآخرة تبعة، برحمتك يا أرحم الراحمين».

“ያ አላህ ሆይ! ድምጾች ሁሉ ላንተ ዝቅ አሉ፤ትእግስቶች ሁሉ አንተ ዘንድ አለቁ፡፡ ሁሉም ነገር ወዳንተ ከጀለ፤ ሁሉም ነገር ከንተ ወዳንተ ሸሸ፡፡ ሁሉም ሙእሚን ባንተ ላይ ተመካ፡፡ አንተ በታላቅነትህ ከፍ ብለሃል፡፡ በዉበትህም ድምበር የለህም፡፡ አንተ በደረጃህ የላቅክ ነህ፡፡ ከሁሉም በላይ ከመሆንህ ጋር ቅርብ የሆንክና ቅርብ ከመሆንም ጋር ከዐርሽ በላይ የሆንክ ሆይ! በስልጣንህም ጠንካራ የሆንክ! በሙሐመድና በሙሐመድ ቤተሰቦች ላይ እዝነትህን አውርድ፡፡ የኣዛኞች ሁሉ ኣዛኝ የሆንከዉ ጌታ ሆይ! በእዝነትህ ካንተ የሆነ ሲሳይን ለግሰኝ፡፡ መመጻደቅንና በመጨረሻይቱ አለም መቀጣትን በሱ ውስጥ አታድርግብኝ፡፡›› ከዚያ በኋላ ወደ ቤት ተመለስኩ፡፡ ወዲያው ታላቅ ሴት ልጄ ወደኔ መጣችና “አባቴ ሆይ! አጎቴ ይህን ቀረጢጥ ሙሉ ብር ይዞ፤ በሱ ላይ ዱቄትን ተሸክሞ፤ በግመል ላይ ደግሞ በገበያ ያለውን ሁሉ ጭኖበት መጣ፡፡ ‹ለወንድሜ ሰላምታዬን ንገሪልኝ፤ የሆነ ነገር ስያስፈልግህ እሄን ዱዓ አድርግ፤ ወዲያው ጉዳይህ ይፈጸማል፡፡› አለ፡፡

አሥበግ ቢን ዘይድም አለ፡- “ወላሂ እኔ አንድም ወንድም አልነበረኝም፤ ይህ ተናጋሪ ማን እንደ ሆነ አላዉቅም፡፡ ነገር ግን አላህ ሁሉም ነገር ላይ ቻይ ነው፤ ምስጋና ሁሉ ለአላህ ለዓለማቱ ጌታ ይገባው፡፡››

ከዚህ ታሪክ የምንማረው ትምህርት፣ ይህ ሰዉዬ ወደ አላህ ተመልሰው ሁለት ረከዓ ሰገደ፤ እጆቹንም ወደ አላህ ዘረጋ፡፡ መፍትሄዉም ወዲያው ከአላህ ዘንድ መጣለት።

አንድ ታሪክ እብን ሐዝም ከአባቱ ዘግቦልን እንዲህ አለ፡- “አንድ ግዜ አቡ መንሱር ቢን ዓሚር ከሰዎች ጋር ተቀምጦ እያለ የሆነ ወረቀት ወደሱ መጣ፤ ወረቀቱ አንድ ልጇ ከታሰረባት እናት ሲሆን ልጁ ባለ ስልጣኑን በማናደደ ወንጀል ነው የታሰረዉ፡፡ ወረቀቱ እዝነትን ይጠይቅለት ነበር፡፡ አልመንሱር ሲያነበዉ የበለጠተናደደ፡፡ ወዲያው አስታውሳችሁኝ ብሎ እንዲገደል ለመፈረም ወረቀት ወሰደ፡፡ ይገደል የሚለውን ለመጻፍ አስቦ ይለቀቅ የሚልን ጻፈ፡፡ ወረቀቱን ወደ ሚኒስቴሩ ሲወረውር ቀለሙን ወስዶ መጻፍ ጀመረ፡፡ አልመንሱርም “ምን እየጻፍክ ነው?›› አለ፡፡ እንዲለቀቅ ነው አለው፡፡ ወረቀቱን በመቀበል የጻፈውን ሰርዞ ‹ይሰቀል› የሚለውን ለመጻፍ ፈልጎ አሁንም ይለቀቅ የሚልን ጻፈ፡፡ ሚኒስቴሩም ወረቀቱን ወስደው እንዲለቀቅ መጻፉን ቀጠለ፡፡አልመንሱርም አየውና “ምን እየጻፍክ ነው?›› አለ፡፡ ልጁ እንዲለቀቅ ነው አለው፡፡ ከመጀመርያው የበለጠ ቁጣ ተቆጥቶ “ማነው በዚህ ያዘዘህ?›› በማለት ወረቀቱን ወስዶ ለሶስተኛ ግዜ በመሰረዝ አሁንም ‹ይሰቀል› የሚልን ለመጻፍ ፈልጎ ‹ይለቀቅ› የሚል ጻፈ፡፡ ሚኒስቴሩም ወረቀቱን ወስዶ ይለቀቅ የሚለውን መጻፉን ቀጠለበት፡፡ “ምን እየጻፍክ ነው?›› አለው፡፡ ልጁ እንዲለቀቅ ነው አለው፡፡ ይህ ንግግር ሶስተኛ ነው፡፡ ይህን ጉዳይ

ሲመለከት ተገረመ፡፡ “እኔ ባልፈልግም ይለቀቃል፤ አላህ እንዲለቀቅ የፈለገዉ ሰው እኔ ምንም ማድረግ አልችልም›› አለ፡፡[1]

ይህን ንጉስ ተመልከት፤ “ይሰቀል›› የሚለውን መጻፍ ፈልጎነበር፡፡ እሱ ቢፈልገዉምአላህ ግን አላሳካለትም፡፡ ይህን ነገር ሶስት ግዜ ሞከረ፤ በመሰረቱ ይህን መጻፍ ይችል ነበር፡፡ አላህ እሱ የሚጽፈውን ፊደል ቀይሮበት ይሰቀል የሚል ቦታ ይለቀቅ የሚለውን ጻፈ እንጂ፡፡ በመጨረሻው ላይ እንዲለቀቅ አዘዘ፡፡ “አላህ እንዲለቀቅ የፈለገዉን ሰው እኔ ልገል አልችልም›› አለ፡፡ አላህ እውነቱን ተናገረ፡ - “አላህም በሰውየውና በልቡ መካከል የሚጋርድ መኾኑን ወደርሱም የምትሰበሰቡ መኾናችሁን እወቁ፡፡›› (አል-አንፋል፡ 24) ይች ሴት ልጇ እንዲለቀቅላት አላህን ለመነች፤ አላህም ተቀበላት፡፡

አቡል ዐባስ አህመድ ቢን አብዱል ሐሊም እንዲህ አለ፡- “ሰዎች ላይ መተግበሯ ግዴታ የማይሆን የአዱንያ ጉዳይን እነሱን መለመን ገዴታም ተወዳጅም አይደለም፡፡ ይልቁንስ የታዘዝነው አላህን መለመን፣ ከሱ መከጀልና በሱ ላይ መመካት ነው፡፡ ሰውን መለመን በመሰረቱ ሐራም ነው፤ ለችግር ነው የተፈቀደ፡፡ በአላህ ላይ ተመክቶ እሱን መተው ይመረጣል፡፡

አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿فَإِذَا فَرَغۡتَ فَٱنصَبۡ ٧ وَإِلَىٰ رَبِّكَ فَٱرۡغَب﴾ [الشرح: ٧، ٨]

“በጨረስክም ጊዜ ልፋ (ቀጥል)፡፡ ወደ ጌታህም ብቻ ከጅል፡፡›› (አሽ-ሸርሕ፡ 7-8).

1- ኢማም ኢብን ሐዝም 80.

አላህን እንጂ ሌላን አትከጅል ማለቱ ነው፡፡ ገጠመኝ ሁሉ ከአላህ ነው፡፡

ተናጋሪው: አብዱላህ ቢን አብዱረሕማን አስ-ሰዕድ

ጻፊው: ሰዕድ ቢን ሙሐመድ አልቀሕጣኒ

24 ዙልቀዕዳ 1427 አመተ ሂጅራ

IslamHouse.com

IslamHouseAM/ Bengali.IslamHouse islamhouse.com/am/

channel/UC0T_q-4JkqIMTfmxa1L3kTw

For more details visit
www.GuideToIslam.com

GUIDE TO ISLAM

contact us :Books@guidetoislam.com

GuidetoIslam.org Guidetoislam1 Guidetoislam www.Guidetoislam.com

المكتب التعاوني للدعوة وتوعية الجاليات بالربوة

هاتف: ٩٦٦١١٤٤٥٤٩٠٠+ فاكس: ٩٦٦١١٤٩٧٠١٢٦+ ص ب: ٢٩٤٦٥ الرياض: ١١٤٥٧

ISLAMIC PROPAGATION OFFICE IN RABWAH

P.O.BOX 29465 RIYADH 11457 TEL: +966 11 4454900 FAX: +966 11 4970126

# ቡርሃን

## አላህን መለመን ግዴታ መሆኑ

ዱዓእ በኢስላም ውስጥ ከፍተኛ ቦታ ያለው ጉዳይ ነው ይህ መጽሃፍ
ዱዓእ የሚለመነው ከአላህ ብቻ ስለ መሆኑ ትምህርት በውስጡ
ይዘዋል አንብበው ዕውቀት እንድቀስሙ ተስፋ እናደርጋለን።




IslamHouse.com
Osoul Center
www.osoulcenter.com